# ኮምቦልቻ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ

## የሰልጣኞች የስነምግባር ደንብ

## /Code of Ethics/

## ሥነ-ስርዓት አፈፃፀም መመሪያ

APPROVED AND CONTROLLED COPY

| | | | |
|---|---|---|---|
| Approval | Name: **Ermias Getnet Assefa (Dean)** | Signature: | Date:14/04/2017 E.C |

# ክፍል አንድ

**መግቢያ**

የሰልጣኝ ስነምግባር በአንድ የተወሰነ ስልጠና ተቋም ስልጠና ለሚወስዱ ሰልጣኞች ህግና ደንብ አክብረው እንዲማሩና በስልጠና ተቋም ውስጥ ሁሉን አቅፍ አዎነታዊ ተሳትፎ እንዲኖራችው፤ ተቋማዊ ሥርዓት፣እንዲሰፍን የስልጠና ጥራት እንዲረጋገጥ እና ምቹ የመማር እና ማስተማር አካባቢን ለመፍጠር የተቋቋሙ ህጎችን፣ እና ደንቦችን ያካተተ ሲሆን ሰልጣኞች የላቀ ስብእና እንዲላበሱና በስልጠና በስራ መስክ ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው። በማሰልጠኛ ተቋም፣ በሙያ ማሰልጠኛ ፕሮግራም ውስጥ፣ የሰልጣኞች ዲሲፕሊን የሰልጣኞችን ባህሪ፣ የስራ ስነምግባር እና አጠቃላይ ሙያዊ እድገት ለመቅረጽ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

**የሥነ-ምግባር መመሪያ ዓላማ**

1. በሥነ-ምግባር የታነጸ ሰልጣኝ ማፍራትና መልካም ሥነ-ምግባር በማስፈን ዉጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማስቻል፡፡
2. የሥነ-ምግባር ጉድለቶች እንዳይፈፀሙ ማስገንዘብ ተፈጽመዉም ሲገኙ እርምጃ ለመዉሰድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፡፡
3. ሰልጣኞች የስነ-ምግባር ደንቦችን በሚገባ አዉቀዉና ተረድተዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ በኮሌጁ ውስጥ ቆይታቸዉ በመልካም ሥነ-ምግባር ተገንብተዉ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
4. ሰልጣኞች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸዉን ያለእንከን ሊመሩ ይቻላቸዉ ዘንድ
5. ስለሥነ-ምግባርና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ምንነት ተረድተዉ ከደንብና ሥርዓት ዉጭ በሚሆኑበት ጊዜ ሊወሰድባቸዉ ስለሚችል እርምጃ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ፡

**የመመሪያው አስፈላጊነት**

ሰልጣኞችን የስነ ምግባር ደንብን እንዲያከብሩ፣መመሪያዎችን እንዲከተሉ፣ እና በስልጠና ሂደቱ ላይ ሙያዊ ብቃት እንዲያሳዩ ማድረግ ነው።

**የሰልጣኞች ኃላፊነትን በተመለከተ**

1. ሰልጣኞች ይህንን የሥነ-ምግባር መመሪያ በሚገባ አዉቀዉ በተግባር ላይ ማዋል አለባቸው፡

2. ሰልጣኞች በኮሌጁዉስጥ ከሥነ-ምግባር ጥስት ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ሲፈጽሙ ለኮሌጁን የበላይ ኃላፊ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. ሰልጣኞች ይህንን መመሪያ የመቀበልና የመፈጸም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## መብቶችና ግዴታዎች

**የሰልጣኞች መብቶች፡**

1. በኮሌጁውስጥ ትምህርትና ስልጠና ባወጣው የስልጠና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በነፃነት የመማር፣የመጠየቅ፣የመመራመር፣የመረዳዳት የማወቅ ሳይንሳዊና ጥበባዊ ክህሎትን የማሳደግ፣ልቆ የመገኘት፤
2. በመማሪያ ክፍል፣በኮሌጁ ግቢና በህብረተሰብ ውስጥ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፡
3. በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ህገ-መንግስታዊና ሰብዓዊ መብታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ የመኖር፡
4. በኮሌጁ ጉዳዮች ላይ በህጋዊና በሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነፃነት የማራመድ፡
5. ማንኛውንም አይነት አድሎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ህጋዊ ከለላን የማግኘት፡
6. በማንኛውም የሰልጣኝና የአሰልጣኝ ግንኙነት የፍትህና ፍትህዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፡
7. ስለአካዳሚያዊ ብቃታቸው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በተደነገጉ መርሆችን በኮሌጁ አካዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን ኢ-ፍትህዊ ምዘና ሲፈፀም ቅሬታን በኮሌጁ ስርዓት መሰረት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትህን የማግኘት፡
8. በትምህርት ማህደራቸው ውስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች በሚስጥር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለፁበት ሁኔታ የሚወስን አስተማማኝ ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፣
9. የሰልጣኙ የጋራ ጥቅሞችን በህጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ህጎች በተቋቋመና የኮሌጁን ሰልጣኞች በሙሉ በአባልነት በሚያቅፈው የኮሌጁ ሰልጣኞች ህብረት አባል የመሆን፡
10. የፈተና ውጤትን በወቅቱ የማየት ቅሬታ ካለ የማቅረብ

11. የፈተና ውጤት / Grade Report/ በወቅቱ የመቀበልና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በማቅረብ አግባብነት ያለው የትምህርት ማስረጃ በግዜ የማግኘት፡
12. ከትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ሀሳቦች የማቅረብ፣የመከራከርና የመወያየት፡
13. ከኮሌጁ ማህበረሰብ ጋር ለሚፈጠሩ ማንኛውም የዲስፕሊን ግድፈቶች (አለመግባባቶች) አግባብነት ያለው ፍትህ የማግኘት እና በተገቢው አካል የመዳኘት፡
14. በኮሌጁ ውስጥ በሚቋቋሙ የሰልጠኞች ክበባትና ሌሎች አግባብነት ባላቸው አደረጃጀቶች (ለምሳሌ የዲስፕሊን፣የመዝናኛ ክበብ የካፍቴሪያ፣የፀረ-ኤድስ፣የጤና የአካባቢ፣የስፖርትና የመዝናኛ ወዘተ…)ውስጥ በአመራርነትም ሆነ በአባልነት የመሳተፍ፣
15. በኮሌጁ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በእኩልነትና በፍትሀዊነት ማግኘት፣
16. በኮሌጁ ህገደንብ/ Legislation/ የተካተቱትን መብቶች በአግባቡ የመጠቀም፡
17. በስራቸውና በችሎታቸው መሰረት ያለምንም አድልዎ የመገምገምና የግምገማዉ ውጤታቸውን የማወቅ፡ቅሬታ ካላቸውም ስርዓትን ተከትሎ የፈተና ወረቀቶቻቸውና የተገመገሙባቸው ስራዎቻቸው እንደገና እንዲታይላቸው የማመልከት ውጤቱንም የማወቅ፤
18. በኮሌጁ ህገደንብ/Legislation/ መሰረት በማንኛውም የመማር ማስተማርና አገልግሎት የሚሰጥበት መስክ በብሄር በፆታ፣በሀይማኖት በፖለቲካ ወይም በሌላ ወገንተኝነት ምክንያት አድልዎ የማይደረግባቸው መሆኑን መረዳት፣ከተደረገባቸውም ለሚመለከተው የአመራር አካል ቅሬታቸውን የማቅረብና ምላሽ ማግኘት፤
19. ቤተ-ሙከራዎችና ወርክሾፖች እንዲሁም ሌሎች ስልጠናቸውን ሊያግዙ የሚችሉ የኮሌጁን ወይም የሌሎች ተቋማትን በሚመለከተው አካል ክትትል የመጠቀም መብቶች አሏቸው፡፡

## የሰልጣኞች አጠቃላይ ግዴታዎች

1. ስልጠና ይጀመራል በተባለው የጊዜ ገደብ በኮሌጁውስጥ በአካል ተገኝቶ የመመዝገብና አስፈላጊውን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ስልጠና የመጀመር፤በክፍል የመገኘትና ስልጠናውን በሚገባ የመከታተል
2. የቲቪ.ኢ.ቲ/TVET/ ዓላማዎችንና የኮሌጁ መሪ እሴቶችን የማወቅና የመተግበር፤
3. አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች የኮሌጁ ፤ የሰልጣኞች ዲስፕሊን መመሪያ ፤ የተቋሙን የትምህርትና ስልጠና ደንብ እንደዚሁም ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸውን ህጎች የማወቅ፤የማክበርና የማስከበር በእነርሱም የመመራት
4. ከማንኛውም ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ- መንግስታዊ መብቶቻቸውን የማክበር
5. የግልም ሆነ የጋራ የሰልጣኞች ጥቅም አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ፍፁም ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ቅሬታን በማሰማት በጋራ መፍትሔ የመሻት፤
6. የኮሌጁን የጋራም ይሁን የግል መገልገያ ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት የኮሌጁን ንብረት ላይ ለሚደርሰው አደጋና ለሚከሰተው ማንኛውም ጉዳት በጋራም ሆነ በግል ተጠያቂ የመሆን እንደዚሁም የደረሰውን ጉዳት የመተካት፤ጥፋት ያደረሰውን አካል የማጋለጥ
7. ኮሌጁ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መክፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም
8. ሁልጊዜ የመገልገያ የመታወቂያ ካርድ መያዘና ለሌላ አካል አሳልፎ ያለመስጠትና በሚመለከተው አካል ሲጠየቁ የማሳየት፤
9. በተመዘገቡበት የስልጠና መስክ የተቀመጡ የብቃት መመዘኛዎችን ማሟላት፤ሪፖርቶችን እና ሌሎች በመምህራን /በአሰልጠኞች / የተሰጡ ስራዎችን በወቅቱ አጠናቆ ማስረከብ
10. በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ለእያንዳንዱ የበቃት አሃድ (የትምህርት ዓይነት ወይም ኮርስ) በሚወጣው ፕሮግራም መሰረት በሌክቸር በላቦራቶሪ በወርክሾፕና በመስክ በመገኘት ስልጠናው የሚጠይቀውን ተግባራትን የማከናወን፤
11. በኮሌጁ የተደነገገውን የመግቢያና የመውጫ ሰዓት ማክበር

12.ማንኛውንም አሰልጣኝ ፣አስተዳደር ሰራተኛ ፣እንዲሁም የማሰልጠንና የአስተዳደር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለውን አካል የማክበር፣

13.ሰልፍ ባለበት ቦታ ሁሉ ሰልፍን ጠብቆ መገልገል

14. ከማንኛውም ህገ ወጥና ከስነ-ምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፣ለምሳሌ ከስርቆት አላግባብ በመጮህ ሌላውን ከማወክለ ሕገ-ወጥ ተግባር ሌሎችን ከማነሳሳት፣ሱስ ከሚያሲዙ (ጫት፣ሲጋራ፣አልኮል ሺሻና የመሳሰሉት) ጎጂ ልማዶች.ወ.ዘ.ተ......ራስንና ሌሎችን የመጠበቅ፣

15. ከኮሌጁ ውጭ ካለው ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት በመልካም ስነ- ምግባር አርአያ መሆን

16. የሌላውን ባህል ቋንቋ፣ሃይማኖት ወዘተ.... ማክበርና መጠበቅ

17. አንድ ሰልጣኝ በተለያዩ ምክንያቶች መባረሩን ሲያውቅ ሰበብ አስባብ ፈልጎ ሌላውን ሰልጣኝ ይዞ ለመጥፋት ያልሆኑ ጥያቄዎችን ማንሳት ሌሎችን መቀስቀስ ረብሻ ለመፍጠር መሞከር፣በማንኛውም ምክንያት ከሌሎች ጋር መጣላትና የመሳሰሉትን ችግሮች ስለሚፈጥር እንደዚህ ዓይነት ሰልጠኞችን ለሚመለከተው አካል ጥቆማ በመስጠት በጊዜ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው የማድረግ፣

18. በሁለት ሰልጣኞች መካከል የሚነሱ ግላዊ ጥሎችን ወደ ብሄርና ሀይማኖት በመለወጥ ግጭት ውስጥ ያለመግባት፣

19.የሚሰጡ የስልጠና የተለያዩ ስራዎችን በራስ ጥረት መስራት፣የሌላው ሰው ስራ የራሱ አስመስሎ አለማቅረብ፣ለሌላ ሰው ሰርቶ መስጠት ወይም ከሌላ ሰው መውሰድ ወይም መኮረጅ የማይቻልና ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን የመረዳት፣

20. ኮሌጁ ውስጥ ባሉ የስልጠና ዘርፎች የሚፈልጉትን የስልጠና አልባሳት (ጋዎነን፣ቱታ እና የመሳሰሉትን) በተጨማሪም የደንነት መጠበቂያ አልባሳትን በአግባቡ ለብሶ መገኘት

21. በኮሌጁ ውስጥ የሰልጣኞችን የግል አለባበስን በተመለከተ ሙሉ ሰውነትን የሚሸፍን ያልተቀዳደደ ልብስና ሽፍን ጫማን የማድረግ ወይም የመጫማት ሴት ሰልጣኞችንም በተመለከተ ከጉልበት በላይ ያጠረ ቀሚስ ከወገብ በላይ እምብርትን እንዲሁም ጡትን አጋልጦ የሚያሳይ ልብስ መልበስ ሌላን ሰው ሊረብሽ የሚችል

ከፍተኛ ሽታ ያለው ሽቶ ዲዮድራንት ሎሽን መቀባት ድምፅ የሚሰጥ ጫማ እና ክፍት ጫማ አድርጎ ቤተ-መፅሐፍት፣ መማሪያ ክፍል እና ቤተ-ሙከራ አካባቢ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው

22. ሰልጣኞች ጠጉር ከመጠን ከ 1.5 ሴሜ በላይ ያለማሳደግ የጠጉር ቀለም ያለመቀባት

23. ማንኛውም ሰልጣኝ ከመማርያዉ ክላስ ውጭ ሄዶ ያለመገኘት፣ሌላ ሰልጣኝን አስከትሎ አለመገኘት

24. በኮሌጁ ግቢ ዉስጥ ምንም ዓይነት ተቀጣጣይ ነገሮችን ያለመያዝ እና ምንም አይነት ሰው ሊጎዳ የሚችል መሳሪያ ይዞ አለመገኘት

25. ማንኛዉም ሰልጣኝ በሌላዉ ሰልጣኝ ላይ ወይ የኮሌጁ ማህበረሰብ ላይ የስነ ልቦና ጫና ሊፈጥር የሚችል መረጃን በወረቀትም ሆነ በማህበራዊ ድህረገፀ በኮሌጁ ዉስጥ ማሰራጨት ፈፅሞ የተከለከ ነዉ

26. ከማንኛውም ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ- መንግስታዊ መብቶቻቸውን የማክበር

## ክፍል ሶስት

### የዲሲፐሊን ግድፈቶችና የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች

1. **<u>በምክር በቃል ማስጠንቀቂያ የሚታለፍ የስነ ምግባር ጉድለቶች</u>**

1.1 በመማሪያ /የስልጠና/ ክፍሎች በጋራ መገልገያ አካባቢዎች ከፍተኛ ድምፅ ወይም ጩኸት ማሰማት ሬዲዮ፣ቴፐ፣ሞባይል የመሳሰሉትን ተጠቅሞ እንደሙዚቃና ሌሎች ድምፆችን በማሰማት የአካባቢን ፀጥታ ማወክ

1.2 በኮሌጁ ግቢ ዉስጥ ሲጋራ ማጤስ፣ በኮሌጁ ግቢ ጠጥቶና ሰክሮ መገኘት

1.3 በኮሌጁ ግቢ ጫት ይዞ መገኘት/ሲጠቀሙ መገኘት

1.4 የኮሌጁን ዉኃና መብራት በአግባቡ አለመጠቀም/ማባከን

1.5 በመማሪያ ክፍል ዉስጥ ማስቲካ ማኘክ/ማስጮህ

**<u>2. የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የስነ- ምግባር ግድፈቶች</u>**

በተራ ቁጥር 1 ከተራ ቁጥር 1.1 እስከ 1.5 የተጠቀሱትን ግድፈቶች ለሁለተኛ ጊዜ ፈፅሞ ሲገኝ/ስትገኝ፡፡

2.1. በኮሌጁ ኃላፊዎች የሚተላለፍን ማነኛዉም ደንብ መጣስ

2.2. የስልጠና ጊዜን በአግባቡ አለመከታተል በተደጋጋሚ ጊዜ መዘግየት

2.3. ከትምህርት ገበታዉ 3ቀን መቅረት፣

2.4. በአሰልጣኝ መምህራን የሚሰጥን የኘሮጀክት ሥራ፣የክፍል ሥራን የቤት ሥራዎችን ወዘተ… በወቅቱ አለመስራት፣

2.5. በኮሌጅ ቅጥር ግቢ ለመግባትም ሆነ ከገቡ በኋላ መታወቂያ ይዞ አለመገኘትና የግቢ መታወቂያን ለሌላ አሳልፎ መስጠት መታወቂያ እንዲያሳዩ ሲጠየቁ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፣

2.6 ባልተፈቀደ መግቢያ መግባትና/መዉጣት

2.7. በኮሌጁ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ ግድግዳዎችና በመሳሰሉት ማንኛዉንም ዓይነት ፅሑፍ መፃፍ

2.8. ሕጋዊ በሆነ መንገድ የተለጠፉ ማስታወቂያዎችን መቅደድ ማንሳት መደለዝ ወይም ማበላሸት

2.9. በፈተና ወቅት በፈተና ወረቀት ላይ ስም ሣይፅፉ ፈተናዉን መስራት መጀመር

2.10. ስፖርታዊ የሆኑ ጨዋታዎችን ቁማር ነክ በሆነ መልኩ መፈፀም

2.11. የኮሌጁን መጽሐፍት ሌሎች እንዳይጠቀሙበት መደበቅ

2.12. ከተለመደዉ ያለባበስ ሥርዓት በወጣ መልኩ ሰዉነትን አጋልጦ መልበስ ፡ በነጠላ ጫማ ወይም ድምፅ በመፍጠር የሚረብሹ ጫማዎችን በመልበስ ፡ ኮፍያ በመልበስ ፡ ቁምጣ በመልበስ ፡ ማስቲካ በማኘክና በማስጮህ ፡ ድምጽን ከፍ አድርጎ በመናገር/በመወያየት ቤተ መጽሐፍት ዉስጥ አንባቢዎችን መረበሽ

2.13. ከክፍል ውስጥ ወንበር አውጥቶ መቀመጥ፡ ውጭ ላይ ወንበር ላይ ተቀምጦ መገኘት፡ በመማሪያ ክፍሎችና ሾፖች ላይ ማንኛውም ዓይነት ጽሁፍ መጻፍ፤ግድግዳዎችን ማበላሸት፡

2.14. ሴት ሰልጣኞችን መሳደብና ማዋረድ እንዲሁም መተናኮስ

APPROVED AND CONTROLED COPY

## ሌሎች ከባድ የዲሲፕሊን እርምጃዎች

| ተ.ቁ | የስነ ስርዓት ግድፈቶች | የሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 3.1 | በተ.ቁ 2 ከተ.ቁ 2.1 እስከ 2.14 የተጠቀሱትን ግድፈቶች ለሁለተኛ ጊዜ ፈፅሞ/ፈፅማ ሲገኝ/ስትገኝ፣ | ለአንድ ሴሚስተር ከስልጠና ማገድ | ለሰልጣኙ የተሰጠው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለሚመለከተው መቅረብ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.2 | በፈተና ወቅት በመፈተኛ ክፍል የፈተና ስነ-ሥርዓት የሚያውክ ማንኛውም ድርጊት፣ | ለአንድ ሴሚስተር ከስልጠና ማገድ | ለሰልጣኙ የተሰጠው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለሚመለከተው መቅረብ ይኖርበታል፡፡ |
| | 3.2.1. መኮረጅ ወይም ከሌላ ሰው መቅዳት | የዕለቱ ፈተና ውጤትም ሆነ ቀደም ሲል የነበረው ውጤት ተሰርዞ ኮርሱን ማስደገም | ፈታኙ የኮራጁንና የአስኮራጁን ወረቀቶች ይዞ መምጣት ይጠበቅበታል፣ ግልጽ ማብራሪያም በአጭሩ ያስቀምጣል፡፡ |
| | 3.2.2. ለማስኮረጅ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ወይም መልስ ጽፎ መወርወር/ማስተላለፍ … | የዕለቱ ፈተና ውጤት ዜሮ ተሞልቶ ቀደም ሲል የተፈተነው ውጤት ብቻ እንዲያዝለት ማድረግ | አስኮራጅ ያደረጋቸውን ሁኔታዎች ማስረዳት ከፈታኙ ይጠበቃል፣ የወረወረ ከሆነ ወረቀቱን ማያያዝ ይጠበቃል፡፡ |
| | 3.2.3. ያልተፈቀዱ ጽሑፎች/አጤሬራ/ ይዞ በመግባት ሲሰሩ መገኘት… | የዚያ ኮርስ ውጤት ሙሉ በሙሉ ተሠርዞ ኮርሱን ማስደገም | አጤሬራው ከፈተና ወረቀቱ ጋር ተያይዞና በፈታኙ ተፈርሞበት ለሚመለከተው ይቀርባል፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 3.2.4. በተመደበበት የመፈተኛ ክፍል አለመገኘት፣ ፈታኙ እንዲቀመጥ በሚያዝዘው ቦታ ለመቀመጥ ፈቃደኛ አለመሆን፤ | ለአንድ ሴሚስተር ከስልጠና ማገድ | በሌላ የመፈተኛ ክፍል ውስጥ ተፈትኖ መገኘቱ መረጋገጥ አለበት በተሰጠው ቦታ ለመቀመጥ ፈቃደኛ አለመሆኑን ፈታኙ በአካል ማስረዳት አለበት፡፡ |
| | 3.2.5. በፈተና ክፍል ውስጥም ሆነ በኮሌጁ ግቢ የፈተናውን ስነ-ስርዓት ለማስከበር ለተመደቡ አካላት ታዛዥ አለመሆን፤ | ለአንድ ሴሚስተር ከስልጠና ማገድ | በዕለቱ/ወዲያው/ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡ |
| | 3.2.6 ፈተና ተፈትኖ የመልስ ወረቀት ሳይሰጡ መውጣት በተፈቀደው ጊዜ እንዲያቆም ተነግሮት እያለ ከተፈቀደው ጊዜ በላይ መጠቀም፣ | ለአንድ ሴሚስተር ከስልጠና ማገድ | ጉዳዩ ፈተናዉ በተሰጠበት ዕለት ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.3 | በኮሌጁ ግቢ እንደ ጩቤ፣ ሽጉጥና መሰል ድምጽ ያላቸውና የሌላቸው ጎጅ መሣሪያዎች ይዞ መገኘት፤ | ለአንድ ዓመት ከስልጠና ማገድ | የተያዘው መሣሪያ በማስረጃነት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.4 | በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ጥል ፈጥሮ መደባደብ | ለአንድ ዓመት ከስልጠና ማገድ | ድብድቡ በተፈፀመበት ዕለት ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡ ጥፋተኛውን የመለየት ሥራ መሠራት አለበት፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.5 | የኮሌጁን አሰልጣኝ መምህር፣ አስተዳደር ሠራተኛ በአጠቃላይ የኮሌጅን ማህበረሰብ አባል መሣደብ ስም ማጥፋት፣ዛቻ፣ በአካልና በሌላ ሰው፣ በስልክ፣ በፖስታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መገላመጥና ማስፈራራት | ለአንድ ዓመት ከስልጠና ማገድ | ከሳሽ ጉዳዩን በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለማጣራት በሚደረግ ሂደትም ሲፈለግ በአካል ቀርቦ በተከሣሽ ፊት ማብራሪያ መስጠት ይኖርበታል፡፡ |
| 3.6 | አግባብ ያልሆነ ባህርይ ማሳየት ኃይል ለመጠቀም መሞከር ጉዳት ማድረስ | ለአንድ ዓመት ከስልጠና ማስወድ | |
| 3.7 | በግል ወይም በቡድን የስልጠና ሂደትን ማወክ | ለአንድ ዓመት ከስልጠና ማገድ | |
| 3.8 | ያልተፈቀዱና ሕጋዊ ያልሆኑ ጹሑፎችን መበተን፤መለጠፍ፤ስብሰባዎችን ማካሄድ፤ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ፤ | ለሁለት ዓመት ከስልጠና ማገድ | |
| 3.9 | ሠልጣኞችን ላልተገባ ዐመፅና አድማ ማነሳሳት፣ማሳደም፣በአመፁ ወይም በአድማዉ መሳተፍ | ለሁለት ዓመት ከስልጠና ማገድ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.10 | የኮሌጁ ንብረት ከሆኑ መፅሐፎች ገጾችን መቅደድ፣መገንጠል፣በላያቸዉ መፃፍ | ያበላሸዉን መፅሐፍ በዓይነት መተካት ወይም ዋጋዉን መክፈልና ለሁለት ዓመት ከስልጠና ማገድ | የቤት መፅሐፍት ሠራተኛ በዕለቱና የተገነጠለዉን/ የተቀደደዉን መፅሐፍ ለሚመለከተዉ አካል ማሳየትና በፅሑፉ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.11 | ሴት ሠልጣኞችን መደባደብ፤በጹሑፍ ወይም በቃል ንግግር ማስፈራራት በተደጋጋሚ ማስቸገር ወይም ማስጨነቅ | ለሁለት ዓመት ከስልጠና ማገድ | ሠልጣኟ ሁኔታዉን በማብራራት ለሚመለከተዉ ክፍል በጹሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.12 | ሴት ሠልጣኞችን አስገድዶ ለመድፈር መሞከር ወይም መድፈር | ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከስልጠና ማሰናበት ከዚህ በላይ የሆኑ እርምጃዎችን ተበዳይ በሕግ ማስፈፀም | ጥቃት ወይም ትንኮሳ የተካሄደበት ሠልጣኝ ሁኔታዉ በግልጽ በመዘርዘር በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.13 | ድምጽ ያለዉ ወይም የሌለዉ መሳሪያ ተጠቅሞ የኮሌጁ ማህበረሰብ አባል የሆነን ግለሰብ ወይም ሰልጣኝ መጉዳት ወይም ለመጉዳት መሞከር | ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከስልጠና ማገድ ከዚህ በላይ የሆኑ እርምጃዎችን ተበዳይ በሕግ ማስፈፀም | ተበዳይ ጉዳዩን በግልፅ ዘርዝሮ በጹሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ |
| 3.14 | ታማኝነት የጎደለው ስነ-ምግባር ምሣሌ፡- መስረቅ ወይም ለመስረቅ መሞከር፣ ማታለል አስመስሎ ለመፈረም መሞከር፣ ውጤትን ደልዞ ወይም አስመስሎ ማታለል ወይም | ለሁለት ዓመት ከስልጠና ማገድና የተሰረቀውን ንብረት ማስመለስ ወይም እንዲተካ ወይም ዋጋውን እንዲከፍል ማድረግ፤ | ጉዳዩ በጽሁፍ ለሚመለከተው አካል መቅረብ ይኖርበታል፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ለማታለል መሞከር፣ የሌላ ሰውን ስራ የራስ አስመስሎ ማታለል ወይም ለማታለል መሞከር፤ | | |
| 3.15 | በተራ ቁጥር 3 ከተራ ቁጥር 3.1 እስከ 3.15 የተጠቀሱትን የስነ-ስርዓት ግድፈቶች የፈፀመው/ችው/ ሰልጣኝ/ተመራቂ ከሆነች በስልጠናው ማጠናቀቂያ የመጨረሻ ሴሚስተር ላይ ከሆነ/ች/ና ሌሎች እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡ | | |
| | ሀ. ለአንድ ሴሚስተር ከስልጠና ማገድ ከሆነ | የትምህርት ማስረጃውን ለ6 ወር መያዝ | |
| | ለ. ለአንድ ዓመት ከስልጠና ማገድ ከሆነ | ለሁለት ዓመት የትምህርት ማስረጃውን መያዝ | |
| | ሐ. ለሁለት ዓመት ከስልጠና ማገድ ከሆነ | ለሦስት ዓመት የትምህርት ማስረጃውን መያዝ | |
| | መ. ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማሰናበት ከሆነ | የትምህርት ማስረጃውን እስከ መጨረሻው መከልከል | |

የሰልጣኞች ጋውን ቀለም

- ቴክስታይል እና ጋርመንት ፣ ሆቴል ____________________ ነጭ
- አይሲቲ ፣ ኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ _________________ ቀይ
- አውቶሞቲቭ ፣ ማኑፋክቸሪንግ___________________________ ጥቁር ሰማያዊ
- ኮንስትራክሽን ፣ ውሃ ቴክኖሎጂ _______________________ ሽሯማ ቢጫ ከለር
- ግብርና ___________________________________________ አረንጓዴ

**የተማሪዎችን የስነ-ምግባር ጉድለቶች ለመመርመርና ውሳኔ**

**<u>ለመስጠት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት</u>**

**<u>ሀ. ሠልጣኙ/ኟ የምትገኝበት የት/ክፍል ተጠሪ</u>**

በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሱት የስነ-ሥርዓት ግድፈቶችን ሰልጣኙ መፈፀሙን ወይም መፈፀሟን ሲገለጽለት ራሱ ወይም የስልጠና አማካሪውን በመጋበዝ ምክር ይሰጣል፤ወይም የቃል ማስጠንቀቂይ ይሠጣል፡፡

1. በተራ ቁጥር 2፣በ2.1፣በ2፣3፣በ2.4፣በ2.5 የተጠቀሱትን ግድፈቶች ለፈፀመ ሠልጣኝ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ በግልባጭ ለአካ/ም/ዲን ያሣውቃል፡፡
2. ምክር/የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠበትን ዕለት ምክሩ/የቃል ማስጠንቀቂያው ሲሰጥ የነበሩ ካሉ ስማቸውን መዝግቦ ይይዛል፡፡
3. ምክር/የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠው መሆኑን ለማረጋገጥ ሰልጣኙን አስፈርሞ ማስረጀውን በጥንቃቄ ይይዛል፤በሚፈለግበት ጊዜ ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፡፡ ምክር/የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠቱን በግልባጭ ለት/ ስልጠና አስተበባሪዉ /አካ/ም/ዲን ያሣዉቃል፡፡
4. ሰልጣኙ ስልጠናዉን አጠናቆ ከመመረቁ በፊት የት/ክፍል ተጠሪዉ ቢዛወር/ስራዉን ቢለቅ ማስረጃዉን ለተተኪዉ ወይም ለሚመለከተዉ አካል የማስረከብ ግዴታ አለበት

በት/ክፍሉ ዉስጥ ያለ ሰልጣኝ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሱትን የስነ ሥርዓት ግድፈቶች ፈፅሞ ሲገኝ  የዲሲፕሊን እርምጃ ለመዉሰድ በሚደረግ ስብሰብ ላይ ይገኛል፣ሀሳብም ሆነ ድምፅ  ይሰጣል፡፡

APPROVED AND CONTROLLED COPY

**ለ. <u>የተማሪዎች/የሠልጣኞች መማክር ስብሰቢ/ተወካይ</u>**

በተራ ቁጥር 3 ከተራ ቁጥር 3.1 እሰከ 3.15 በተጠቀሱት የዲሲፕሊን ግድፈቶች ላይ በሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች ላይ ብቻ ተገኝቶ ሀሣብም ሆነ ድምፅ ይሰጣል፡፡

**ሐ. <u>የት/ስልጠና የስራ ሂደት አስተባባሪ /የአካ/ም/ዲን</u>**

በተራ ቁጥር 2 በት/ክፍል ተጠሪዉ በኩል እንዲፈፀሙ ከተጠቀሱት ዉጪ ያሉትን ግድፈቶች ለፈፀመ ሠልጣኝ ጉዳዪ ሲቀርብለት የጽሑፉ ማስጠናቀቂያ በግሉ ይሰጣል፡፡ በግልባጭ ለዲን ጽ/ቤትና ለት/ክፍል ተጠሪዉ ያሳውቃል፡፡

በተራ ቁጥር 3 ከተራ ቁጥር 3.1 እሰከ 3.15 የተጠቀሱ ግድፈቶች መፈፀማቸዉ ሲገለጽለት የሚመለከታቸዉን አካላት ስብሰባ ይጠራል ስብሰባዉንም ይመራሉ በስብሰባዉም የተደረሰበትን የዉሣኔ ሀሳብ ለዲኑ በፅሑፍ ያቀርባሉ፡፡

በተራ ቁጥር 3 ከተራ ቁጥር 3.1 እሰከ 3.16 በተጠቀሱት ግድፈቶች ውስጥ ግድፈት የፈፀመ ሰልጣኝ ጉዳይ ሲቀርብለት እጅግ ቢዘገይ ባንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሚመለከታቸውን ክፍሎች ስብሰባ ጠርቶ የውሳኔ ሀሳብ በማስጠት ለዲኑ ያቀርባል፡፡

**መ. <u>የትምህርትና ስልጠና የስራ ሂደት</u>**

ይህ አካል በተ.ቁ 3 ከተቁ 3.1 እስከ 3.16 ከተጠቀሱት የዲሲፕሊን ግድፈቶች ዉስጥ በሰልጣኞች መፈፀማቸዉን በት/ስልጠና የስራ ሂደት አስተባባሪው ሲቀርብለት በጉዳዩ ተወያይቶ የዉሳኔ ሃሳብ ለኮሌጁ ዲን እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

**ሠ. <u>የኮሌጁ ዲን</u>**

የኮሌጅ ዲን የት/ስልጠና የስራ ሂደት ያቀረባቸዉን የዉሳኔ ሃሳቦች መርምሮ ያሻሽላል ያፀድቃል የመጨረሻ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

# ክፍል ሶስት

## አጠቃላይ የሥነ-ምግባር መርሆችና የዲስፐሊን ጥፋቶች

- ቅንነት
- ግልፅነት
- ታማኝነት
- ምስጢር ጠባቂነት
- ሐቀኝነት
- ህግን ማክበር
- አርአያነት
- ተጠያቂነት
- ህጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል
- ለህዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት

- **ቅንነት**

**በቅንነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የኮሌጁ ክብርና ዝና የሚጎዳ፣ የሰልጣኙንና የተቋሙን ማህበረሰብ የሚያዉክ ባህሪይና ተግባር መፈጸም ወይም ማሳየት፣

ለ. የኮሌጁን ህግና ደንብ በመጣስ ሱስ በሚያስይዝ መድሃኒት ወይም በአደንዛዥ እፅ ሱስ በመመረዝ ወይም በልማዳዊ መጠጥ ተጽእኖ ምክንያት ስልጠናን በአግባቡ አለመከታተልና ተገቢ ያልሆነ አድራጎት መፈጸም፣

ሐ. በግልና በማህበራዊ ህይወታቸዉ ኮሌጁንና የኮሌጁን ማህበረሰብ መልካም ግምትና አመኔታ የሚያሳጣ ድርጊት መፈጸም

መ. የተሳሳተ መረጃን በተለይም ለአዲስ ገቢ ሰልጣኞች በመስጠት ህገ-ወጥ ተግባራትን መፈጸም፡፡

- **ግልፅነት**

**በግልፅነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ህጋዊ ለሆኑ ከኮሌጁና ከኮሌጁ ማህበረሰብ ለሚቀርብ ጥያቄ ግልጽ ምላሽ ወይም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን

ለ. የኮሌጁ የሰልጣኞች መማክርትና የተለያዩ ክበባት ለሚያስተላልፉት ዉሳኔ ተገቢዉን ማብራሪያ ወይም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን

ሐ. ሰልጣኞች ከስልጠና ገበታቸዉ ለቀሩባቸዉና ለሚቀሩባቸዉ ቀናት ህጋዊና ግልጽ መረጃ ለሚመለከተዉ አካል አለማቅረብ

መ. ህጋዊና ግልጽ ባልሆኑ መንገዶች ወደ ግቢ መግባት ወይም መዉጣት ወይም ንብረት ማዉጣት ወይም ማስገባት

- **ታማኝነት**

**በታማኝነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የሀገሪቱንና የኮሌጁን ህግና ደንብ አለማክበር

ለ. በኮሌጁ በሰልጣኞች ወይም በሌላ አካል የሚደረግ ህገ-ወጥ እንቅስቃሴን እያወቁ በጊዜ አለማጋለጥ ወይም ተባባሪ መሆን፡

ሐ. በማንኛውም አጋጣሚ ከኮሌጁ የተረከቡትን ማንኛዉም ዓይነት ንብረት ወይም መገልገያ በጥንቃቄ አለመያዝና ማበላሸት፣

መ. የኮሌጁን ማህበረሰብ ንብረት መስረቅ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፣

ሠ. በኮሌጁ የሚገኙ ወይም የሚሰጡ የጋራ አገልግሎቶች እንደ ሻዉር፣ ሽንት ቤት፤ ቤተ-መጽሀፍት፣ የመሳሰሉትንና ሌሎች አገልግሎቶች የጋራ መገልገያ ስለሆኑ በግል ብቻ ወይም በቡድን ብቻ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር፡

ረ. የሌሎችን ስራ እንደራስ አድርጎ ማቅረብ ወይም ለማቅረብ ማሞከ ያስቀጣል፡

- **ምስጢር ጠባቂነት**

**በምስጢር ጠባቂነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡

ሀ. ሰልጣኞች በትምህርት ቆይታቸዉ ከሙያቸዉ ጋር በተያያዘ መልኩ ወይም ከኮሌጁ ሥራ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚያዉቋቸዉን ሚስጢሮች አለመጠበቅና የኮሌጁን መልካም ስም ማጉደፍ ያስቀጣል፡፡

- **ሐቀኝነት**

  **በሐቀኝነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

  ሀ. የተለያዩ የማጭበርበር ወንጀሎችን መፈጸም ወይም ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ፣ ለምሳሌ፣አስመስሎ መፈረም፣ህጋዊ የሆኑ ሠነዶችን መሠረዝ፣መደለዝና አሰመስሎ መሥራት፣

  ለ. ፈተናን መኮረጅ፣ማስኮረጅ፣ከደብተር ወይም ከወረቀት መገልበጥ ወይም መሥራት ወይም የፈተና ወረቀትን ደልዞ ወይም ጨምሮ አሰልጣኝን በህገ ወጥ መንገድ ዉጤት ለማስቀየር መሞከር፣

  ሐ. ጉቦ በመስጠት ዉጤትን ለማስቀየር መሞከር ፣

  መ. በኮሌጁ ዉስጥ ለሚደረጉ ነገሮች በሀሰት መመስከር፣

  ሠ. በኮሌጁ ክሊኒክ መድሀኒቶችን ለሌላ ተግባር ማዋል፣

  ረ. የኮሌጁንመታወቂያ ካርድ ወይም የአገልግሎት መለያ ካርድ ለሌላ ግለሰብ አሳልፎ መስጠት

- **ህግን ማክበር**

  **በህግን ማክበር** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

  ሀ. በኮሌጁ የሚወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን አለማክበርና አለመከታተል፡፡

  ለ. በኮሌጁ ውስጥ ስልጣን ባለዉ አካል የሚወጡ ልዩ ልዩ ደንቦችን ለምሳሌ እንደ የቤተ-መጽሐፍ የቤተ-ሙከራ የወርክ ሾፕ እና ሌሎች ደንቦችን በቸልተኝነት ሆን ብሎ መጣስ፣

  ሐ. በህጋዊ መልኩ የተባረረን ሰልጣኝ ወደ ግቢዉ ውስጥ ማስገባት

  መ. ህጋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ዉስጥ መበተን ወይም ማሰራጨት፣

  ሠ. ማንኛዉም ሰልጣኝ ማሟላት የሚገባዉን ነገር አልተደረገልኝም ብሎ ሲያስብ በግል ወይም በተወካዩ አማካይነት በህጋዊ መንገድ ማቅረብና ምላሽ ማግኘት ሲገባዉ ራሱንም ሆነ ሌሎችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለአመጽ ማነሳሳት፣

ረ. በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ያልተፈቀደ ስብሰባ ማካሄድ፣አድማ ማሳደም፣ለማሳደም መሞከር፣ህገ-ወጥ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ወይም ለማድረግ መሞከር፣

- **አርአያነት**

በአርአያነት ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ/ ሰልጣኞች በኮሌጁ ቆይታቸዉ በመልካም ሥነ-ምግባር ግንባር ቀደም በመሆን የሚጠበቅባቸዉን መልካም አርአያነት አለማሳየት እና በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መርሆች አለማክበር ወይም መጣስ፣

ለ/ ሰልጣኞች በኮሌጁ ቆይታቸዉ የኮሌጁ ስምና ክብር የሚያቀል መተማመንና መልካም አንድነት የሚያጠፋ ተግባርና እንቅስቃሴ ላይ መሰማራት፣

ሐ/ ሰልጣኞች በኮሌጁ ቆይታቸዉ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ እና በሀይልና በጉልበት ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን ከኮሌጁ ማህበረሰብ ጋር መመስረት፣

- **ተጠያቂነት**

**በተጠያቂነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ለግጭት የሚገፋፉና አሰነዋሪ የሆኑ ነገሮችን በቃል ወይም በጽሁፍ በመማሪያ ፣በመጸዳጃ በቢሮዎች ግድግዳዎች፣በመዝጊያዎች፣ በመስኮቶችና በቁም ሳጥኖች ላይ መጻፊ፣ስዕል መሳል ወ.ዘ.ተ. ያስቀጣል፡፡

ለ. ሥር የሰደደ የጥላቻ ባህሪይ በኮሌጁ ማህበረሰብና በአካዳሚክ ስታፍ ላይ ማሳየት ወይም ማንጸባረቅ፡

ሐ. የኮሌጁን ሠራተኞችና አሰልጣኞች መልካም ስምን በሀሰት በጹሁፍ ወይም በሌላ መንገድ ሊያጎድፍ የሚችል ድርጊቶችን መፈጸም፡፡

መ. በመደራጀትና ረብሻን በማነሳሳት የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች እንዳይካሄዱ ማድረግና የኮሌጁንየስራ እንቅስቃሴ ማስተጎጎል፡፡

ሠ. በኮሌጁ ግቢ ዉስጥ በዘር፣በብሔር፣በፖለቲካ ልዩነት፣በሃይማኖት፣ በቀለም ክፍፍል ወ.ዘ.ተ. ፈጥሮ መሳደብ መደባደብና ግጭቶችን መፍጠር

ረ. በምዘና ወቅት ከወረቀት መስራትና ይህንን ሊያስቆሙ ከሚንቀሳቀሱ ፈታኝ አሰልጣኞች/ግለሰብ ጋር ግብግብ መፍጠር ወይም ለመደባደብ መሞከር

ሰ. በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ሴት ሰልጣኞችን አስገድዶ መድፈር ወይም ለመድፈር ሙከራ ማድረግ፣

ሸ. ከኮሌጁ አሰልጣኞችና ሠራተኞች ጋር እንዲሁም እርስ በርስ ጥል ፈጥሮ መደባደብ፣መሳደብና ማንጓጠጥ፣

ቀ. በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ድምጽ ያለዉን ወይም የሌለዉን የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘትና ጉዳት ለማድረስ መሞከር

በ. ሴት ሰልጣኞችን በንግግር፣ በጽሁፍ፣በኃይል ወ.ዘተ. ማስፈራራት፣ መዝለፍ፣ ማስቸገር ፣ማስጨነቅና ወሲባዊ ትንኮሣ ማካሄድ፣

ተ. የሰልጣኙን ሥነ አእምሮ ሊጎዱ የሚችሉ ኃይለ-ቃሎችን በመጠቀም (ለምሳሌ ሴት ሰልጣኞችን ፣የአካል ጉዳትን፣የሰዉነት አቋምን፣ከባህል ጋር ግንኙነት ያላቸዉን ነገሮች ወዘተ) ምክንያት በማድረግ ሰልጣኙ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማዉ ማድረግ

ቸ. የኮሌጁ የጋራ መገልገያ ቁሳቁሶችን ማበላሸት ለምሳሌ መዝጊያ ፣ መስኮት፣በር፣የዉሃ ቧንቧዎችንና የሻዉር ዕቃዎችን መስበርና ማበላሸት እንዲሁም የመጻህፍት ሰነዶችን መቅደድ እና መስረቅ

ነ. የኮሌጁን ንጽህናና ጽዳት የሚጎዱ ድርጊቶች፣ለምሳሌ አበቦችን መንቀል አጥር ማፍረስ፣ በመማሪያ ክፍሎች አካባቢ ሽንት መሽናት ወይም መፀዳዳት፣

ኘ. በላይብረሪና በመማሪያ ክፍሎች አከባቢ ሌሎችን በሚያዉክ መልኩ ድምጽን ከፍ አድርጎ መጮህ ወይም መነጋገር፤

አ. በኮሌጁ ግቢ ዉስጥ ግልጽ የሆነ ወሲብ ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ መያዝ

- **ህጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል**

**ህጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የኮሌጁ መማክርት አባላትና የሰልጣኞች ክበባት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች በአግባቡ እንዲገለግሉ የተሰጣቸዉን ኃላፊነት በህግ ከተሰጣቸዉ የስልጣን ገደብ ዉጭ አላአግባብ መጠቀም፤

ለ. የመማክርት አባላትና የክበባት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች ሥራቸዉን ከህግና ደንብ ወይም መመሪያን መሠረት በማድረግ አለመሥራት ፤

ሐ. የሰልጣኞች መማክርት አባላትና የክበባት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች ሥልጣናቸዉን የግል ጥቅም ለማግኘት ማዋል፤

- **ለህዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት**

ለህዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ሰልጣኞች በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ዉስጥ በሚኖሩት/በስልጠና ላይ እያሉ ወቅት በሀገራዊና በአከባቢያዊ በሆኑ አንገብጋቢና አስቸኳይ ሁኔታ ተፈጥሮ ከመንግስትና ከአከባቢ ማህበረሰብ በሚቀርቡ የድጋፍና የትብብር ጥያቄዎችን መተባበር እየተቻለ ሆን ተብሎ ጥያቄዎን አለመቀበልና የዜግነት ምላሽ አለመስጠት ፡

## ክፍል አራት

### መረጃ በመስጠት መተባበር

**በጥቆማ ስለማሳወቅ**

1. ማንኛዉም ሰልጣኝ በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተካተቱትን መርሆዎችን የሚጻረር የሥነ-ምግባር ጉድለት መፈጸሙን በማንኛዉም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለሚመለከተዉ ክፍል ማሣወቅ አለበት
2. የሚያቀርበዉ ጥቆማ እዉነተኛ፣ ያልተዛባ፣ ከበቀል የፀዳ፣ አሣሣች ያልሆነ ምክንያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ጥቆማ አቅራቢዉ ከማንኛዉም የበቀል ጥቃት የመጠበቅ መብት አለዉ፡፡
4. ጥቆማ አቅራቢዉ ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ ማንነቱ በሚስጢር መያዝ አለበት፡፡

**የመተባበር ግዴታ**

ማንኛዉም ሰልጣኝ ለዲስፕሊን ሥራ የሚያስፈልገዉንና የሚጠየቀዉን መረጃ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡